# በኑረንበርግ ከተማ የተካሄደው የሰብአዊ መብት ሕዝባዊ ስብሰባ

# በተሳካ ሁናቴ ተጠናቀቀ







ቅዳሜ ጥቅምት 29 ቀን 2007 ዓ.ም. (ኖቬምበር 8 ቀን 2014 ዓ.ም.) ታሪካዊነት ባላት በኑረንበርግ ከተማ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ደጋፊ በሆኑ ኢትዮጵያዊያን የተዘጋጀው በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ሁናቴ ላይ ውይይት ለማድረግ የተዘጋጀው ሕዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን ከቦታው የደረሰን ዜና ያመለክታል። ይህ በአይነቱ የመጀመሪያው የሆነው ዝግጅት በርካታ ወጣት ኢትዮጵያዊያንና እንዲሁም ለሰብአዊ መብት ተከራካሪ የሆኑ የጀርመን ዜጎች በተገኙበት የተካሄደ ሲሆን ለውይይት የቀረበው ዋና ርዕስ „የሰብአዊ መብት ሁናቴ በኢትዮጵያ“ የሚል ነበር።

በዚሁ የውይይት ዝግጅት ንግግር እንዲያቀርቡ በክብር እንግድነት የተጋበዙት የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ሊቀመንበር የሆኑትና ላለፉት በርካታ አመታት ለሰብአዊ መብት መከበር በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት፡ በደርግ ፋሺስታዊ አገዛዝ የተካሄደውን የቀይ ሽብርን አሰቃቂ ግድያ፡ እንግልትና በደልን „የትውልዱ ትውስታዎች“ በተሰኘ ርዕስ በፊልም ቀርፀው ለሕዝብ እይታ በማቅረብ አድናቆትን የተቆናጸፉት፡ በተለያዩ ለምሳሌ „አበቦች ለ እስር ቤት“ ፡ „እሪ አበል አበሻ“ ና ሌሎችም ግጥሞቻቸው ተወዳጅነትንና ታዋቂነትን ያተረፉት የተከበሩ አሊ ሁሴን፡ እንዲሁም በዚሁ መስክ የአባታቸውን ፈለግ በመከተል በካናዳ በመንቀሳቀስና የዊኒፔግ ከተማ የክብር ሽልማት ባለቤት የሆነቺው ወጣት ምሳሌ ሰኢድ ነበሩ።



ስብሰባው የተከፈተው በወጣት ግሩም አለሙ ሲሆን በቅድሚያ ጥሪ ለተደረገላቸውና በእንግድነት ለተጋበዙት የጀርመን ዜጎች በጀርመንኛ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት በማቅረብና ስለ ኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ አጠር ያለ የመግቢያ ንግግር ነበር። በማስከተልም በጀርመንኛና በአማርኛ ለታዳሚዎች በሰብአዊ መብት መጠበቅ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ስለምትገኘው ወጣት ምሳሌ ሰኢድን ለውይይቱ ተካፋዮች በማስተዋወቅ ንግግሯን እንድታቀርብ ወደ መድረኩ በወጣት ግሩም አለሙ ተጋበዘች።

ወጣት ምሳሌ አሊም ለተደረገላት ጥሪ አዘጋጆቹን ከልብ በማመስገን ሀገራችንና ሕዝባችን በአሁኑ ወቅት በሚገኙበት ሁናቴ እንደ ወጣት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል? በሚለው ጥያቄ በመነሳት ገለፃዋን ለታዳሚው እንደሚከተለው አሰምታለች።

*„እህትና ወንድሞቼ እና የስብሰባው አዘጋጆች*

*በመካከላችሁ ላይ ተገኝቼ በሰብአዊ መብት ጉዳይ ላይ እንደ አንድ ወጣት የግሌን አስተያየት እንድሰጥ በመጋበዜ ከልብ አመሰግናለሁ።“*



*„ወደ ነጥቤ ልግባና አሁን ባለው የሀገራችን ሁናቴና የሰብአዊ መብት ረገጣ ወጣቱ ምን ሊያደርግ ይገባዋል? ድርሻውስ ምንድነው? ብዬ ስመለከት ቀደም ሲል ሀገራችንን ከውጭ ጠላት ማለትም ከጣልያን ፋሺስት በመከላከል ያቆዩ ወጣቶች ናቸው። የኃይለ ሥላሴ መንግስትን ከሥልጣን እንዲወርድ ያደረጉ ወጣቶች ናቸው። ከባርነት ብዙውን ሕዝብ ነፃ የሚያወጣውን የመሬት ይዞታ እንዲቀየር የታገሉት ወጣቶች ናቸው። የብሄርና ብሔረሰብ፡ እኩልነት እንዲኖር ሁሉም በእኩልነት፡ በአንድነት እንዲኖር የታገሉ ወጣቶች ናቸው። ጨፍጫፊና ዲክታተር የሆኑ የፋሺስት ቡድኖችን የታገሉ ጀግኖቹ ወጣቶች ናቸው። ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ለሀገራቸው ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል። ብርቅዬ ሕይወታቸውን ሰጥተዋል። ሬሳቸው በመንገድ ላይ ተጥሏል። „*

በመቀጠልም

*„ወያኔን ገና ሲገባ ያጋጠመው የወጣቶች ተቃውሞ ነው። በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲኖር ወጣቶች ብዙ ታግለዋል። መስዋዕትነት ከፍለዋል። በ 1997 በወያኔ ጥይት የተቆሉትን ወጣቶች ምንጊዜም የምንረሳቸው አይደሉም። ስለዚህም አሁን ሕዝባችን ያለበት ሁኔታ በጣም ግፍ የበዛበት፡ ልጆቹ የተደፈሩበት፡ ሀገሩ ለሕንድ፡ ለቻይና፡ ለአረብ የተሸጠበት፤ ለሱዳን የተሰጠበት፡ ረሃብ በላይ ላይ የነገሰበት፡ ባጠቃላይ እንደ አንድ ሰው መታየት ያልቻለበት ሁነታ ላይ በመሆኑ ከምንጊዜውም ፊቱን ወደኛ ወጣቱ በመመልስ እየጠራን ነው። ስለዚህም በተለያዩ የፖለቲካና የሲቪል ድርጅቶች ውስጥ በመግባት መብቱን ለማስከበር አቅሙ፡ እውቀቱና ቴክኖሎጂው ስላለን ተሳታፊ በመሆን መታገል አለብን ። ለዚህም ደግሞ አመቺ የሆነውና ብዙ ልምድ ያለው ሶሴፐ ስለሆነ ይህንን የሰብአዊ መብት ኮሚቴ ማጠናከር የበለጠ ቀላልና ምቹ በመሆኑ እጅ ለጅ ተያይዘን የድርሻችንን እናበርክት እያልኩ ንግግሬን እጨርሳለሁ።“*

*„አመሰግናለሁ*

*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!“* በማለት ከደመደመች በኋላ የአማርኛ ቋንቋን ለመናገር ለማይችሉት ተሰብሳቢዎች በእንግሊዝኛ መልዕክቷን ገልፃለች።

በመቀጠል ወጣት ግሩም አለሙ ለተጋበዙት የጀርመን እንግዶች በጀርመንኛ ቋንቋ ስለ ኢትዮጵያና በተለይም ደግሞ ስለ ወያኔ የአገዛዝ ሥርአት ይዘት፡ ስለ ሃሳብ ነፃነት፡ ስለ ሬዲዮ ስርጭት፡ ስለመሬት ለባዕዳን መቸብቸብ፡ ከቀዬ ስለመባረርና ለስደት መዳረግ፡ ስለ ረሃብና ድህነት፡ ኃይልን በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ ስለመጠቀም፡ ስለታሰሩ የፖለቲካና ጋዜጠኞች ሁናቴ በኮምፑተር በተቀረፀ ስዓላዊ ገጽታና መረጃ የተደገፈ ገለጻ በጀርመንኛና በአማርኛ በስፋት ለተሰብሳቢው አቅርበዋል። ወጣት ግሩም ገለጻውን ካጠናቀቀ ገለፃ በኋላ አቶ አሊ ሁሴንን ለተሰብሳቢው ማንነታቸውን በማስተዋወቅ ከመድረኩ ቀርበው ንግግራቸውን እንዲያሰሙ በትህትና ጋበዘ።

የተከበሩ አቶ አሊ ሁሴንም ይህንን የዛሬውን የውይይት ስብሰባ ላዘጋጁት የላቀ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። እንዲሁም በዚሁ መድረክ ላይ ተገኝተው ንግግር ለማድረግ ስለተጋበዙና እድሉን በማግኘታቸው የተሰማቸውን ልባዊ ደስታ በመግለፅ ገለፃቸውን እንደሚከተለው ለታዳሚው አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ሊቀመንበር አቶ አሊ ሁሴን በቅድሚያ እሳቸው በሊቀ መንበርነት የሚመሩት ኮሚቴያቸው መቼ፡ ለምንስ እንደተቋቋመና ከተቋቋመብት ጊዜ አንስቶም እስካሁን ድረስ የሰራቸውን በርካታ ተግባራት እጥር ምጥን ባለ ሁናቴ አንዳንዴም በተወዳጅ ግጥማቸው በማጀብ ለታዳሚው ገልፀዋል። በተለይም በወያኔ አገዛዝ ስለታሰሩት ዜጎች ስላላቸው የብሄር፡ የኃይማኖትም ሆነ የፆታ፡ የዜግነትም ሆነ የፖለቲካ አስተያየትና አቋም ኮሚቴያቸው ከግምት ሳያስገባ ኮሚቴያቸው ለነታምራት ላይኔ ለነ ሥዬ አብራሃ እንኳ ሳይቀር እንደተንቀሳቀስ ነገር ግን ከነሱ ምንም አይነት ምላሽ እንዳላገኘ በመጥቀስ በማስከተልም በተለያዩ የጎረቤት ሀገር በመዝለቅ እስር ቤት በመግባት የታሰሩ ዜጎቻችንን ለመጠየቅና ለመርዳት፡ አልፎ ተርፎም ወደ ሶስተኛ ሀገር ለመሄድ ሁናቴው እንዲመቻችላቸው ያደረጋቸው ጥረቶች ስኬታማ እንደሆኑ፡ በምሥራቅ አካባቢ ለዘመናዊ ባርነት ለተዳረጉ ሴቶቻችንና ስደተኞችም ሲቻል በቦታው በመገኘት ሳይቻል ሲቀር ደግሞ ለመንግሥታቱና ለሚመለከታቸው ሰብአዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች አቤቱታ በማቅረብ ችግራቸው እንዲቃለል ያልተቆጠበ ጥረት ማድረጉን፡ ሰፋ ባለ ሁናቴ ገልፀዋል። በፌብሩዋሪ 2014 ዓ.ም. የኢትዮጵያ የአየር መንገድ ምክትል አብራሪ ኮፓይለትና የ 31 አመት እድሜ የነበረው ኢትዮጵያዊ ዜጋ አውሮፕላኑ መስመሩን እንዲቀይር በማስገደድ ከስዊዝ ሀገር እንዲያርፍና የፖለቲካ ጥገኝነት በጠየቀበት ወቅት ፈጥኖ ጠበቃ በመያዝ ጥያቄው እንዲሟላለት የመጀመሪያው ደራሽ እንደሆነበረም ገልፀዋል። ኮሚቴው ደብዛቸው ለጠፋው ለነፀጋዬ ደብተራውና ለሌሎችም ዜጎቻችን እንዲሁም የቀይ ሽብር ታሪክ አለማቀፋዊነት ይዘት ያለው በመሆኑ በዊኒፔግ ከተማ በቅርቡ በተመረቀው ሙዚየም የድርጊቱ ሰለባ የሆኑ ስማቸውና ታሪካቸው እንዲሁም ፎቶአቸው እንዲቀመጥ ያደረጋው ከፍተኛ ጥረት መሳካቱን እንዲሁም ይህ በአይነቱ ልዩ የሆነ ስኬት ለሰላምና ለሙብት መከበር የሚንቀሳቀሱትን ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የሚያኮራ እንደሆነም በፎቶግራፍ ማስረጃ በማስደገፍና አፅንዖት በመስጠት ለተሰብሳቢው ገልፀዋል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ተግባሩን እስካሁን ድረስ በማካሄድ ላይ የሚገኘው ሀገር ወዳዶችና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቀናኢነት ባላቸው ኢትዮጵያዊያንና የሰላም ወዳድ ኃይሎች በሚያደርጉለት እርዳታና ትብብር በመሆኑ ምስጋና ብቻ ሳይሆን ሊረዳም እንደሚገባው በመግለፅና ልብን ማራኪ የሆነ ግጥም በማሰማት ለአድማጮቻቸው ይህንን ኮሚቴ በተቻላቸው መጠን በአባልነትም ሆነ በገንዘብ አስተዋፅዖ እንዲረዱት አፅንዖት የተሞላበት ጥሪያቸውን በማቅረብ ንግግራቸውን ቋጭተዋል። በርግጥም በወሬ ሳይሆን በተግባር የታሰበን አላማ ባለ

አቅምና በፅናት ስኬታማ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ለተባባሪዎቹ ቀርቶ ለሚሰማው እንኳ የልብ ኩራት የሚሰጥ እንደሆነ ተስተውሏል። በነካ እጃችሁ ቀጥሉበት የሚል ምክር የሰጡ ከስብሰባው ተካፋዮች የተሰነዘረ አስተያየት ነበር።




ለዚህ ስብሰባ ታቅደው የተሰሩ በቅርቡ በግብር ይውጣ የተገደሉ መሆናቸው ይፋ የተደረጉት የኢሕአፓ ከፍተኛና የድርጅቱ ከፍተኛ እርከን አመራር አባላት የፎቶ ምስላቸው የሚታይበት ካኒቴራ የተዘጋጀ ብቻ ሳይሆን ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት በግፍ የመገደላቸውን ቁጭት ለማስታወስና ሀዘኔታቸውን የገለፁበት ጥቁር ጨርቅ የስብሰባው አዘጋጆች በክንዳቸው ላይ በማሰር ታዳሚዎችን መቀበላቸውና ዝግጅቱንም ማስተናገዳቸው፡ ከመድረኩ ጀርባ በጥቁር ጨርቅ የታጀበ የፀጋዬ ደብተራው ፎቶ ከመሰቀሉ ጋር ተዳምሮ የእለቱ ትዕይንት የደመቀ እንዲሆን አስተዋፅዖ ማበርከቱ ተስተውሏል። የአበራሽ በርታ ፎቶም ከመድረኩ መሰቀሉም ተስተውሏል።



በዝግጅቱ ሂደትም በፎቶ የተዘጋጁ ትዕይንቶች በተለይም በካናዳ ዊኒፔግ ከተማ አዲስ በተገነባው ሚዜየም የቀይ ሽብር ሰለባዎች ፎቶና ሥም ያለበት ለተሰብሳቢው እይታ ቀርበዋል። ይህ ሁናቴ የበርካታዎችን ሕሊና እንደሳበም በጥያቄና መልስ ውይይቱ ወቅት የቀረቡት ጥያቄዎች አመላክተዋል።



ከዚሁ ጋር በተያያዘ ስለ ሰብአዊ መብት የሚገልፁ በእንግሊዝኛ የተፃፈው 30 አንቀፆችን የያዘው፤ በፎቶግራፍ መልክ የተዘጋጁ በወያኔ አገዛዝ የተካሄዱ የሰብአዊ መብት ጥስቶችን የሚያሳይና እንዲሁም በዩኔስኮ ተዘጋጅቶና በአማርኛ የተተረጎመ Universal declaration of Humna Rights ስለ ሰብአዊ መብቶች ለማስተማር የሚረዱ አንዳንድ ዘዴዎች ተጠርዘው ለተሰብሳቢው ተሰራጭተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የነፀጋዬንና የትግል ጓዶኞቹን ኢሰብአዊ ግድያ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ያወጣው መግለጫም በጀርመንኛ ተተርጉሞ እንዲሰራጭም ተደርጓል። እንዲሁም የተለያዩ ሲዲዎችና መጽሃፍቶች ለሽያጭ ቀርበው ነበር።

 

 

ከክብር እንግዶቹ ገለፃ በኋላ ለጥያቄና መልስ ሰፋ ያለ ጊዜ በመስጠት የሃሳብ ልውውጦች ተደርገዋል። ከተሰብሳቢውና እንዲሁም ከአንድ የሀገራችንን የፖለቲካ ሁናቴ በቅርበት ከሚከታተል ጀርመናዊ የሕግ ጠበቃ የማበረታቻ ሃሳቦች የተሰነዘሩ ብቻ ሳይሆን የገንዘብ አስተዋፅዖም ተደርገዋል። ተመሳሳይ ሕዝባዊ ስብሰባ በሌሎች የጀርመን ከተሞች እንዲሚዘጋጅም ለማወቅ ተችሏል። በመጨረሻም ለክብር እንግዶቹ ለአቶ አሊ ሁሴንና ለወጣት ምሳሌ አሊ የእቅፍ አበባ ከአዘጋጆቹ ተበርክቶላቸው የእለቱ ትዕይንት ተፈጽሟል። ተመሳሳይ ዝግጅት በእንግሊዝ ሀገር በለንደን ከተማ በሚቀጥለው ቅዳሜ የሚካሄድ በመሆኑ የኮሚቴው ሊቀመንበር አቶ አሊ ሁሴን በማግስቱ ጉዟቸውን ወደ እንግሊዝ ሀገር አቅንተዋል።

ኑረንበርግ 08.11.2014 ዓ.ም.